# አቶ አርከበ እቁባይ የት ይሆን ያሉት ?

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)

ግንቦት 12

## ትልቅ ቅሬታ በዘካፒታል ኢትዮጵያ በሚባለዉ ጋዜጣ ላይ

አቶ ታዬ ተክለማሪያም (ኩማ ደመቅሳ) የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባነትን በቅርብ ይረከባሉ ተብሎ ይጠበቃል። አቶ ታዬን እንደ "ተምራጭ" ከንቲባ አድርገዉ የሚያቀርቡ አንዳንድ ጋዜጠኖች አልጠፉም። "ዘ ካፒታል ኢትዮጵያ" የሚባለዉ ኢትዮጵያ የሚታተም የእንግሊዘኛ ጋዜጣ "አዲስ አበባ የመጀመሪያ ተመራጭ ከንቲባዋን አገኘች ሲል ነበር የዘገበው። [1]

ነገር ግን ሃቁና እዉነታዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሸሸገ አይደለም። የአዲስ አበባ ህዝብ የሚያዉቀዉ ከንቲባ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ብቻ ነዉ።፡ በምርጭ ዘጠና ሰባት የአዲስ አበባ ሕዝብ ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ እንዲስተዳድረዉ ነበር በማያሻማና በማያወዛግብ መልኩ ድምጹን የሰጠዉ።(ከ 138 መቀመጫዎች 137 ያሸነፈዉ ቅንጅት ነበር። )

ቅንጅት የአዲስ አበባን መስተዳደር ተርክቦ ማስተዳደር ያልቻለዉ ዘ ካፒታል የተሰኘዉ ጋዜጣ አሳፋሪ በሆነ መልኩ እንደዘገበዉ ቅንጅት በተገቢዉ ሆኔታ መደራጀት ስላልቻለ ሳይሆን ሕወሃት/ኢሕአዴግ የሕዝብን ድምጽ ረግጦና ህዝብ ለመረጣቸዉ የቅንጅት አባላት ሥልጣን አላስረክብም ስላለ፣ ዘግናኝ ግፍ በሞላበት መልኩ የቅንጅት አመራር አባላትን በማሰሩና በማንገላታቱ ነበር። ከወዲሁ ሕዝባዊ የሆነን ንቅናቄ ለማፈን እነ አቶ መለስ/ስብሃት/በረከት ስለወሰኑ ነበር። አቶ ስብሃት ቅንጅት ጠላት ነዉ ያሉትን ማስታወስ ይበቃል። (ቢያንስ ቢያንስ እነዚህ ነጻ ነን የሚሉ እንደ ዘ ካፒታል አይነት ጋዜጦች በእዉነት ላይ የተመሰረተ ዘገባ ቢያቀርቡ መልካም ነበር። አለበለዚያ አርፈዉ ይቀመጡ። ለዉሸትና ለፕሮፖጋንዳማ እንደነ አይጋ ፎረምና ሮፖርተር ያሉ ያሰለችን ብዙ አሉ)

## አቶ ኩማ ደመቅሳ ሳይሆኑ አቶ መለስ ዜናዊ ናቸዉ ከንቲባዉ

ታዲይ በቅርቡ ተደረገ በተባለዉ የማሚያ ምርጫ ሕወሃት/ኢሕአደግ አሸነፈ ተብሎ የሚነገረን ነገር ከቀልድና ከጨዋታ ዉጭ ቦታ የሚሰጠዉ ጉዳይ አይደለም። ማንም ሰዉ፣ የሚያስብና ጭንቃላት ያለዉ ከሆነ በአዲስ አበባ ተደረገ የተባለዉን ጆክ ምርጫ አድርጎ የሚቆጥር አለ ብዬ አላስብም። አቶ መለስና ጓዶቻቸዉ እራሳቸዉን ባያታልሉ ይሻላቸዋል። አቶ ታዬ ተክለማሪያም ሕዝብ የመረጣቸዉ ሳይሆኑ በአቶ መለስ ዜናዊ የተሾሙ ከንቲባ ናቸዉ።

አቶ ታዬ ተክለማሪያም ከስምንት አመታት በፊት ከነ አቶ ስዬ አብርሃም ጋር በነበረዉ ዉዝግብ ወደ ዳር እንደተገፉ የሚታወስ ነዉ። በኋላ እንደሳሙና ተሞላልጨዉ ከአቶ አባይ ጸሃዬ ጋር ይቀርታ ጠይቀዉና እንደገና አቶ መለስ ዜናዊ ላለመካድ ተገዝተዎዉ ነዉ ወደ አምባገነኖቹ ክበብ የተቀላቀሉት።

ስለዚህ አለአንዳች ማቅማምት አቶ ታዬ ተክለማሪያም ሙሉ ለሙሉ የአቶ መለስ ጥገኛ እንደሚሆኑ የታወቀ ነዉ። በሌላ አባባል የአዲስ አበባ ከንቲባ እራሳቸዉ አቶ መለስ ዜናዊ ናቸዉ ማለት ይቻላል።

## አቶ አርከበ እቁባይ ለምን እንደገና አልተሾሙም ?

ይልቅ ለሕወሃት የሕዝብ ድጋፍ ትንሽም ብትሆን ለማግኘት ቢፈልጉ ኖሮ አቶ ታዬን ሳይሆን አቶ አርከበ እቁባይን የቀድሞ የአዲስ አበባን ከንቲባ ነበር መሾም የነበረባቸዉ። እርግጥ ነዉ አመራር አባል

---

[1] http://www.capitalethiopia.com/archive/2008/may/week3/local_news.htm#1

በመሆናቸዉና ግፍ ሲሰራ ዝም በማለታቸዉ አቶ አርከበ እቁባይ ላይ ትልቅ ጥያቄ ምልክት አድርጌባቸዋለሁ። ነገር ግን የአዲስ አበባ ከንቲባ የነበሩ ጊዜ ባሳዩት አንጻራዊ

ዉጤቶች ከሚያደንቁዋቸዉ ሰዎች መካከል አንዱ ነኝ። የአዲስ አበባ ሕዝብ ለእርሳቸዉ ትልቅ ከበሬታ እንደነበረዉ ሰምቻለሁ። አንድ ወቅት ታክሲ ነጆዎችን ጥርተዉ ሰብስባ ባነጋገሩበት ወቅት “ቅንጅት ሁንና እንመርጥሃለን” ብለዋቸዉ እንደነበረ ይወራ ነበር። በማዘጋጃ በት የሚሰራ አንድ ወዳጄ እንደነገረኝም አቶ

አርከበ ብዙ ጊዜ እስከ ምሽቱ አራት ሰዓት በቢሮዋቸዉ ሲሰሩ ያመሹ ነበር።

ታዲያ አቶ መለስ ቀልድ በሆነ ምርጫ “ሕዝብን አታልላለዉ” ብለዉ እራሳቸዉን ከሚያታልሉ፣ ለመሾም ለመሾም ከሆነ አቶ አርከበን ቢሾሟቸዉ ለሕወሃት/ኢሕአዴግም መልካም ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ።

አቶ አርከበ በአቶ መለስ እንደገና ላለመሾማቸዉ የተለያየ ምክንያት ሊሰጥ ይችል ይሂናል። አቶ አርከበ እቁባይ እንደገና የአዲስ አበባ ከንቲባ ላለመሆን ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርቶ ግን አይመስለኝም፡፤ እንደምገምተዉ ከሆነ አቶ መለስ የአቶ አርከበን “ታማኝነት” ጥያቄ ምልክት ዉስጥ ሳያስገቡት የሚቀር አይመስለኝም። የአቶ አርከበ ከአዲስ አበባ ህዝብ ጋር “መዛመድ”፣ በተራ ሕወሃት አባላት ዘንድ ያላቸዉ ተሰሚነትና በአስተዳደር ያካበቱት ልምድ … ያለምንም ጥርጥር አምባገነኑ አቶ መለስ ዜናዊን ማስጋቱ አይቀርም። የሥልጣን ጉዳይ ነዉና !!!

አምባገነኖች ከማንም የበለጠ አብረዋቸዉ ያሉትን ሰዎች ነዉ የሚጠራጠሩት ? ለሥልጣናችን ይቀናቀነኑናል የሚሉትን ሁሉ መግደል፣ ማሰር አሊያ ወደ ግዞት አምባሳደር አድርጎ መሾም ዋነኛ ዘዲያቸዉ ነዉ። ኮሎኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም ብርጋዴር ጀነራል ተፈሪ ባንቲ፣ ጄኔራል አማን አንዶም፣ ኮሎኔል አጥናፉ አባተን

በጭካኔ አላስወገደም እንዴ ? እንደዚሁም አቶ መለስ ጄኔራል አየሎም እንዲሁም አቶ ክንፈ ገብረ መድህንን በዘዴ እንዳስወገዷቸዉ ነዉ የዉስጥ አዋቂዎች የሚናገሩት። ጄኔራል ጻድቃን ገብረስላሴ የቁም እስረኛ ሆነዋል። እነ አቶ ስዬ አብርሃምና፣ አቶ ገብሩ አስራት ያሉበትን ሆኔታ ሁላችንም የምናወቀዉ ይመስለኛል።

ስለሆነም አቶ መለስ ዜናዊ ነገ ሊነክሳቸዉ የሚችለዉን ዉሻ አሁን መቀለብ አይፈልጉም። አቶ አርከበ ከሕዝብና ከአባላት ፊት ማስወገዳቸዉ መጠነኛ እፎይታ ሳይሰጣቸዉ አይቀርም።

የአቶ አርከበ ቀጣዩ እርምጃ ምን ሊሆን እንደሚችል ወደፊት የምናየዉ ነገር ይሆናል። እንደ አቶ ስዩም መስፍንና አባይ ጸሃዬ፣ ፊሪና ለፕሪንስፕል ያልቀሙ ደካማ ሆነዉ፣ በረከሰና በአሳዛኝ ሆኔታ ይቀጥሉ፤ ወይንስ አንድ ወቅት የሚወዳቸዉና የሚያከብራቸዉን ሕዝብ ድምጽ ሰምተዉ ለአምባገነኖች ሳይሆን ለህዝብ ጥቅም ይቆማሉ ? ሕወሃት ከሕዝብ እያጣላዉ ያለዉን የአቶ መለስ ዜናዊ ከፋፋይ ፖለቲካ አካል ሆነዉ ያቀጥላሉ ወይንስ “አሁንስ በቃ” ብለዉ ለዉጥ እንዲመጣ ይጥራሉ ? ይህን በቅርብ ጊዜ ዉስጥ የምናየዉ ጉዳይ ይሆናል ?

ለአቶ አርከባ አይነቶቹ ግን ያለኝ መልእክት በዝምታ የሚቆዩበት ጊዜ እያለቀ እንደሆነ ነዉ። **ኢትዮጵያዉያን ከሁሉም አቅጣጫ ጸረ-ኢትዮጵያዊ የሆነዉን የእነ አቶ መለስ/ስብሃት/በረከት ፖለቲካ ለመቀየር ከፍጻሜ ለማድረስ የጨከኑበት ጊዜ ነዉ። ማእበሉ እየመጣ ነዉ። ሕዝብ እጅግ መሮታል። አብራችሁ ተጠራርጋቹህ ማዕበሉ ከሚያጠፋቹህ የማዕበሉ አካል መሆኑን ብትመርጡ ሳይበጃችሁ አይቀርም።** የኢትዮጵያ ህዝብ ይቅር ባይና ልበ ሰፊ ነዉ።